# የቀኖና መጻሕፍት እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን

## ሀ. የቀኖና መጻህፍት የሚባሉት ምን አይነት መጻሕፍት ናቸው?

ቀኖና የሚለው ቃል «ካኖን» ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ነው፤ ትርጉዋሜውም መለኪያ ማለት ነው፤ በዋናነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተወሰኑትን ድንጋጌዎች በሙሉ ሲያመለከት ከመጻህፍት አንጻር ሲነገር ግን ስልጣን ያላቸውን የብሉይና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ያመለክታል፤ የኢትዮጵ ያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለእነዚህ መጻሕፍት «መጻሕፍት አምላካውያት» የአምላክ መጻሕፍት የሚል ስያሜ ሰጥታቸዋለች፤

እነዚህ መጻሕፍት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሰበኩ ሊነበቡና ሊጠኑ የሚገባቸው መጻህፍት ሲሆኑ በሃይማኖት ነገር የመጨረሻ ምስክር ናቸው፤ ይህን ሥልጣን ቤተ ክርስቲያን ለእነዚህ መጻህፍት የሰጠችውም በእስትንፋሰ እግዚአብሔር የተጻፉ መጻሕፍት ስለሆኑ ነው፤ በእስትንፋሰ እግዚአብ ሔር የተጻፉ የሚለው ቃል፤

1. ጸሐፊውን እግዚአብሔር አምላክ እየመራ አጽፎአቸዋል፤
2. ጸሐፊውን እግዚአብሔር ከስህተት ሁሉ ጠብቆታል።
3. በመጻሕፍቱ ላይ አንዳችም ስህተት የለም
4. መጻሕፍቱን እግዚአብሔር ከጥፋት ጠብቆአቸዋል፤ የሚለውን ሐሳብ ይሰጣል፤

## ለ. እስትንፋሰ እግዚአብሄር የተባሉት የቀኖና መጻህፍት በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ለምን ተለ ያየ፤

እስትንፋሰ እግዚአብሔር የተባሉትን መጻህፍት በዋናነት ለመለየት ከፍተኛ ችግር የተፈጠረው በ ብሉይ ኪዳን መጻህፍት ላይ ነው፤ ይህም ያለምክንያት አይደለም፤ ሰባ ሊቃናት በተረጎሙት የብ ሉይ ኪዳን መጻህፍት ውስጥ የሚገኙት መጻህፍቶች በስደት ባሉት አይሁድ በግሪክ ቋንቋ ብቻ እ ንጂ በእብራይስጥ ስላልተገኙ በኢየሩሳሌም ያሉ የአይሁድ ሊቃውንት ጃሚኒያ በተባለ ቦታ 90 ዓ .ም ባደረጉት በቀኖናቸው አልተቀበሉአቸውም ነበር፤ በቀኖናቸው ያልተቀበሉአቸውን መጻህፍት ኢያሮኒሙስ (ጀሮም) የተባለው የቤተ ክርስቲያን አባት አፖክሪፋ ትርጉሙም ድብቅ የሚል ስያ ሜ ሰጣቸው፤ የቤተ ክርሰቲያን አባቶች ስለእነዚህ መጻህፍት ያላቸው አስተያየት ለሁለት የተከፈ ለ ነው፤ አንዳንዶች የአይሁድን ቀኖና ሲከተሉ ሌሎች ደግሞ የሰብአ ሊቃናትን ዝርዝር ተከትለ ዋል።

## ሐ. . የቤተ ክርስቲያናችንን የቀኖና መጻሕፍት ቁጥርን ስናጠና የሚያጋጥሙን ችግሮች

1. ስለ ቀኖና መጻህፍት ያለን አስተሳሰብ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት በተለየ የላላ መሆኑ፤
2. የቀኖና መጻህፍት 81 ናቸው ቢባልም ወደዚህ ቁጥር በተለያዩ መንገዶች መድረሳችን፤ የመጽሀ ፉ በዝርዝሩ ላይ መቀመጥ የመጽሀፉን በሰዎች መገኘት አለማረጋገጡ፤
3. የቀኖና መጻህፍት የሚባሉት በግእዝም ሆነ በአማርኛ ታትመው አለመገኘታቸው፤ የታተሙትን ም የቤተ ክርስቲያን አባቶች የተሙዋላ ነው አለማለታቸው፤

መ. የቀኖና መጻህፍቶቻችን ዝርዝር ምንጮች፤

ሲኖዶስና ፍትሀ ነገስት፤ ሲኖዶስ በሚል ስም የሚታወቀው የቤተ ክርስቲያናችን መጽሀፍ የመጀመ ሪያዎቹን የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት ውሳኔዎች የሚዳስስ መጽሀፍ ነው፤ ፍትሀ ነገስት በተለይ የ ቀኖና መጻህፍትን ጉዳይ በዳሰሰበት አንቀጹ ላይ ምስክር ያደረገው ሲኖዶስን ነው፤ በዚህም ምክን ያት ሁለቱም መጻህፍት ያላቸው ዝርዝር ተመሳሳይ ነው።

በአጠቃላይ በቤተ ክርስቲያናችን ያሉትን የቀኖና መጻህፍት ዝርዝሮች በሁለት አበይት ክፍሎች ልንከፍላቸው እንችላለን፤ እነርሱም ረጅሙ ዝርዝርና አጭሩ ዝርዝር በሚል ነው፤

<u>ረጅሙ ዝርዝር</u>

ለዚህ ምንጭ የሆነን የፍትሐ ነገሥት የአማርኛው አንድምታ ነው፤ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብ ሎ የሚዘረዝራቸው ህግ (5) ኢያሱ መሳፍንት ሩት ዮዲት መጽሀፈ ነገስት (4) ዜና መዋእል (2) እዝራ (2) መጽሀፈ አስቴር መጽሀፈ ጦቢት መጽሀፈ መቃባውያን (2) ኢዮብ (1) መዝሙረ ዳዊት (1)መጻሕፍተ ሰሎሞን (5) ነቢያት (16) ሲራክ (1) ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን (1) መጽሐፈ ኢዩቤልዩና ሄኖክ የተከተቱት በአቆጣጠር ነው። (ይህም ሳሙኤልንና ነገሥትን እንደ ሁለት መጻሕፍት በመቁ ጠር ነው፤ የአዲስ ኪዳን መጻህፍት ብሎ የሚዘረዝራቸው ወንጌል (4) የሐዋርያት ሥራ (1) አጠ ቃላይ መልእክታት (7) የጳውሎስ መልእክታት (14) የዮሀንስ ራእይ (1) ሲኖዶስ (4) መጽሐፈ ኪ ዳን (2) ቀሌምንጦስ (1) ዲድስቅልያ (1)

ይህን አቆጣጠር በተለያየ መንገድ የሚከተሉ የቅርብ አባቶች መጻህፍት

- የመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ ኮኩሃ ሃይማኖት
- የሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ መርሃ ልቡና
- የልዑል ራስ ካሣ ሀይሉ ፍኖተ አእምሮ
- የሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (አሁን አቡነ መልከ ጼዴቅ) የኢትዮጵያ ኦርቶ ዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት
- የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የህዝቅኤል ትርጉዋሜ ናቸው።

<u>አጭሩ ዝርዝር</u>
በዓጼ ኃይለ ሥላሴ ትእዛዝ የታተመው መጽሐፍ ቅዱስና መጽሐፈ ቅዳሴ አጠር ያለውን ዝርዝር ይዘዋል።ይህም ዝርዝር የተለመዱትን 39 የብሉይ ኪዳን መጻህፍት መጽሀፈ ምሳሌን ለሁለት በ መክፈል 40 ሲያደርሳቸው ከእነዚህ በተጨማሪ ሄኖክ ኢዩቤልዩ ጥበብ እዝራ እዝራ ካልእ ዮዲ ት ጦቢት ባሮክ ተረፈ ኤርምያስ ሶስና ተረፈ ዳንኤል 1ኛና 2ኛ መቃቢስ በአጠቃላይ 54 የብሉይ ኪዳን መጻህፍት ከ27 የአዲስ ኪዳን መጻህፍት ጋር 81 ያደርጋቸዋል።

ይህን ዝርዝር የተከተሉ

- ትልቁ የአማርኛ መጽሀፍ ቅዱስ
- የብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደ ስላሴ ጎሀ ጽባህ
- የአስረስ የኔሰው የካም መታሰቢያ፤

## በረጅሙ ዝርዝር የተካተቱ ነገር ግን በህትመት ላይ ያልዋሉ መጻህፍት

1. መጽሀፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን (መጽሐፈ ሥርው) ዜና አይሁድ ተብሎ የሚታወቅ፥ በስምንትክፍል የተከፈለ ሲሆን በምእራቡ አለም «ጆሴፋስ» ተብሎ በሚታወቀው ታሪካዊ ስራላይ የተመሰረተ ነው፤

2. ሲኖዶስ፤ የቤተ ክርስቲያን የሥርዓት መጽሐፍ ነው፤ በትውፊት ሐዋርያት እንደጻፉት የሚነገረው ይህ መጽሐፍ በአራት ክፍል ይከፈላል፤ ሥርዓተ ጽዮን (30 ቀኖና) ትእዛዝ (ሰባ ቀኖና) ግጽው (56 ቀኖና) አብጥሊስ (81 ቀኖና)

3. ቀሌምንጦስ፤ በሰባት ክፍል የተከፈለና ቅዱስ ጴጥሮስ ለወራሹ ለቀሌምንጦስ የጻፈው ነው፤

4. መጽሐፈ ኪዳን እንደ ሁለት የሚቆጠር ሲሆን የመጀመሪያው ስድሳ ምእራፍ ስለ ሥርዓተቤተ ክርስቲያን ነው፤ ሁለተኛው ክፍል ክፍል ስድሳ አንድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሳኤ በሁዋላ በገሊላ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀምጦ ያስተማራቸውን የሚናገር ነው፤

5. ዲድስቅልያ፤ በ43 ክፍሎች የተከፈለ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መጽሐፍ ሲሆን በሌላው ዓለም ከሚታወቀው «ሥርዓተ ሀዋርያት» ተብሎ ከሚታወቀው መጽሐፍ ጋር ተመሳሳይነትአለው፤

## ማሳሰቢያ

ይህ አጭር ጽሑፍ በቀኖና መጻህፍት ዙሪያ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያላትን ሀሳብ ለማሳየት ነው፤ አጠቃላይ አብያተ ክርስቲያናት ስለቀኖና መጻሕፍት ያላቸውን ልዩነትና ይህም እንዴት ሊመጣ እንደቻለ በሰፊው በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጥናታችን ላይ ልናየው እንችላለን፤

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ኦርቶዶክሳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መለያ ባህርያት ከሆኑት ሶስቱን በራሳችሁ አነጋገር ግለጡት፤ (እያንዳንዱ ከአራት አረፍተ ነገር አይብለጥ)
2. መጽሐፍ ቅዱስን በተለያዩ ክፍሎች መክፈሉ ለምን ይጠቅማል?
3. ቀኖና መጻሕፍት የምንላቸው ከሌሎች መጻህፍት የሚለዩት በምንድነው?
4. የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያዎቹን አምስት መጻህፍት ምን ይባላሉ ታሪካቸው በጥቅሉ ምን ምንን ያጠቃልላል።
5. በኦሪት ዘፍጥረት ከሚገኙት ሰዎች ውስጥ የአራቱን ብርቱና ደካማ ጎን ዘርዝሩ ፤
6. ኦሪት ዘፍጥረት ለእናንተ የሚሰጠው ጥቅም ምንድነው? (በማስታወሻ ላይ የተገለጠ ውን ሳይሆን ግላዊ እይታችሁን ግለጡ)